# የግሉ ዘርፍ ድምፅ

የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት በሀገራችን የንግድና ኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ ውስጥ ቁልፍ ሚና ለሚጫወተው የንግድ ማህበረሰብ ከሀምሌ 1 ቀን 2017 ዓ.ም ጀምሮ በስራ ላይ የዋለውን የፌደራል የገቢ ግብር ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 1395/2017አስመልክቶ ይህንን የግንዛቤ ማስጨበጫ ሰነድ አዘጋጅቷል። በአዋጁ በግብር ስርዓቱ ላይ በርካታ ማሻሻያዎች እንዲሁም አዳዲስ የታክስ አሰባሰብ ስርአቶች የተዋወቁ ሲሆን የግብር ከፋይ ማህበረሰብ ሊያውቃቸው የሚገቡ ዋና ዋና ነጥቦች ከዚህ በታች እንደሚከተለው ተሰንደው ቀርበዋል።




**የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት**

**Ethiopian Chamber of Commerce and Sectoral Association**

**ሜክሲኮ አደባባይ፣ አዲስ አበባ**

**+251-115-514005**

info@ethiopianchamber.com

**www.ethiopianchamber.com**


# የኢትዮጵያ የፌዴራል የገቢ ግብር (ማሻሻያ) አዋጅ (1395/2025) ላይ የተደረጉ መሰረታዊ ለውጦች

## ለንግድዎ መመሪያ

## አዲስ የግብር ከፋይ ደረጃዎች፡ ደረጃ 'ሀ' ወይስ 'ለ'?

የቀድሞው ሶስት የግብር ከፋይ ደረጃዎች (ሀ፣ ለ ፣ ሐ) ተሰርዞ በአዲሱ አዋጅ ደረጃ 'ሀ' እና 'ለ' በሚል ተተክቷል፡፡ በመሆኑም በማሻሻያው አዋጅ መሰረት ግብር ከፋዮች በሚከተሉት ደረጃዎች ውስጥ የሚካተቱ ይሆናል፡፡

### ደረጃ 'ሀ' ግብር ከፋይ (Category A) የሚባለው፡

- ድርጅት(ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበራት፣ አክሲዮን ማህበራት፣ ወዘተ) ወይም
- ጠቅላላ ዓመታዊ ገቢው ብር 2 ሚሊዮን ወይም በላይ የሆነ ማንኛውም ሌላ ሰው ሲሆን

**ማሳሰቢያ፡** ሁሉም የሙያ አገልግሎት ሰጪዎች (አማካሪዎች፣ የሂሳብ ባለሙያዎች፣ ጠበቆች፣ ወዘተ) በዚህ ምድብ ውስጥ እንዲካተቱ እና የተሟላ የሂሳብ መዝገብ እንዲይዙ ይጠበቅባቸዋል።

### ደረጃ 'ለ' ግብር ከፋይ (Category B) የሚባለው፡

- ድርጅትን ሳይጨምር ዓመታዊ ጠቅላላ ገቢያቸው ከብር 2 ሚሊዮን የሚያንስ ሰው ነው፡፡

## ከዲጂታል አገልግሎት እና ዲጂታል ይዘት ፈጠራ የሚገኝ ገቢ

የግብር መሰረትን ከማስፋት እንዲሁም ፍትሀዊ የንግድ ስርአት ከመዘርጋት አንጻር ከዲጂታል አገልግሎት እንዲሁም ከዲጂታል ይዘት ፈጠራ የሚገኝ ገቢ በማሻሻያው አዋጅ መሰረት ግብር የሚከፈልበት ይሆናል፡፡ በዚህም መሰረት የዲጂታል ይዘት አመንጪዎች የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር የማውጣት፤ ገቢን የማስታወቅ እና ሌሎችም የታክስ ከፋይ ግዴታዎች ይኖሩባቸውል፡፡

### ሀ. የዲጂታል አገልግሎት ግብር (አንቀጽ 53) በተመለከተ፤

በኢትዮጵያ ውስጥ የዲጂታል አገልግሎት በመስጠት ገቢ የሚያገኝ ነዋሪ የሆነ ወይም ያልሆነ ማንኛውም ሰው የገቢ ግብር የሚከፍል ሲሆን የግብር መጠኑ ከ5% የማይበልጥ ሆኖ ዝርዝር አፈጻጸሙ በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ የሚወሰን ይሆናል።

### ለ. ከዲጂታል ይዘት ፈጠራ የሚገኝ ገቢ (አንቀጽ 22) በተመለከተ፤

ከዩቲዩብ፣ ከማህበራዊ ሚዲያ፣ ከፖድካስት እና መሰል የኦንላይን መድረኮች የሚገኝ ገቢ፣ መደበኛ የንግድ እንቅስቃሴ አካል ሆኖ ሲገኝ እንደ ንግድ ገቢ ታክስ ይጣልበታል። ይህ ካልሆነ ግን "ሌሎች ገቢዎች" በሚል ከጠቅላላ ገቢው ላይ 15% ግብር ይከፈልበታል።

## አማራጭ አነስተኛ ግብር (አንቀጽ 23)

አማራጭ አነስተኛ ግብር ደረጃ 'ሀ' ግብር ከፋዮችን የሚመለከት ሲሆን በዚህ ደረጃ ያሉ ግብር ከፋዮች ግብር በሚወሰንበት የግብር አመት ከሁሉም የንግድ ስራ የገቢ ምንጮች ባገኙት ትርፍ ላይ ሊከፍሉ የሚገባቸው ግብር በዚሁ የግብር አመት ካገኙት ጠቅላላ ገቢ ከ 2.5 % (በመቶ) በታች ከሆነ ከዚህ እንደሚከተለው በተመላከተው የማስከፈያ ምጣኔ መሰረት

- የማናቸውም ድርጅት ወይም ሰው ከሆነ ከአመታዊ ጠቅላላ ገቢው 2.5 በመቶ፤
- ባንኮችን በሚመለከት ከባንክ ስራ የተገኘ የተጣራ ገቢ 2.5 በመቶ፤
- የኢንሹራንስ ኩባንያዎችን በሚመለከት ከህይወት እና ከህይወት ውጪ ከሆነ ኢንሹራንስ የተገኘው ጠቅላላ አረቦን 2.5 በመቶ እንዲሁም
- ዋጋቸው የተወሰነ እቃዎችን አቅራቢ ድርጅትን በሚመለከት የኮሚሽን ገቢው 2.5 በመቶ አማራጭ አነስተኛ ግብር የሚከፍሉ ይሆናል፡፡

## በመቀጠር የሚገኝ ገቢ የግብር ተመን (አንቀጽ 11)

በማሻሻያው አዋጅ መሰረት በመቀጠር በሚገኝ ገቢ ላይ የሚጣለው የገቢ ግብር ተመን ተሻሽሏል። ይህ ማሻሻያ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸውን የህብረተሰብ ክፍሎች ተጠቃሚ ለማድረግ ያለመ ሲሆን፣ የግብር ማስከፈያ ምጣኔዎች በሰንጠረዡ እንደሚከተለው ቀርቧል፡-

| በየወሩ ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ (በብር) | በመቀጠር በሚገኝ ገቢ ላይ ተፈፃሚ የሚሆን ምጣኔ (በመቶኛ) |
|---|---|
| 0 - 2,000 | 0% |
| 2,001 - 4,000 | 15% |
| 4,001 - 7,000 | 20% |
| 7,001 - 10,000 | 25% |
| 10,001 - 14,000 | 30% |
| ከ14,000 በላይ | 35% |

## የኪራይ ገቢ ግብር ተመን (አንቀጽ 14)

በግለሰቦች የኪራይ ገቢ ላይ የሚጣለው የገቢ ግብር ተመን ላይ ማስተካከያ ተደርጓል። የግብር ማስከፈያ ምጣኔዎች በሰንጠረዡ እንደሚከተለው ቀርቧል፡-

| ዓመታዊ ግብር የሚከፈልበት የኪራይ ገቢ (በብር) | የኪራይ ገቢ ግብር ምጣኔ (በመቶኛ) |
|---|---|
| 0 - 24,000 | 0% |
| 24,001 - 48,000 | 15% |
| 48,001 - 84,000 | 20% |
| 84,001 - 120,000 | 25% |
| 120,001 - 168,000 | 30% |
| ከ168,000 በላይ | 35% |

**ማስታወሻ፡** በማሻሻያው አዋጅ (አንቀጽ 15(8))መሰረት "ከቤት ኪራይ የሚገኝ ገቢ" ማለት ለማናቸውም አገልግሎት ከሚውል ህንጻ፣ ከመኖሪያ ቤት፣ ለመጋዘን አገልግሎት ከሚውል ህንፃ ኪራይ የሚገኝ ገቢ ሲሆን የኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚ የሚገነባቸውን የኢንዱስትሪ መሰረተልማቶች እና በካፒታል ዕቃ ኪራይ ንግድ ስራ መሰረት የንግድ ስራ ሀብት ሆነው የሚከራዩ ህንጻዎችን ወይም ግሪን ሃውስ እና በመጋዘን ውስጥ ዕቃ የሚያከማቹ ሰዎች የሚከፍሉትን ክፍያ **አይጨምርም፡፡**

## የደረጃ “ለ” ግብር ከፋዮች ግብር አከፋፈል (አንቀጽ 50)

በደረጃ "ለ" የተመደቡ ግብር ከፋዮች ግብር የሚከፍሉ በግብር አመቱ ውስጥ ከእቃ እና አገልግሎት ሽያ ጠቅላላ የሽያጭ ገቢ ላይ ሲሆን የግብር ማስከፈ ምጣኔዎች በሰንጠረዡ እንደሚከተለው ቀርቧል፡-

| ግብር የሚከፈልበት ዓመታዊ ጠቅላላ የሽያጭ ገቢ (በብር) | ምጣኔ (በመቶኛ) |
|---|---|
| 0 - 100,000 | 2% |
| 100,001 - 500,000 | 3% |
| 500,001 - 1,000,000 | 5% |
| 1,000,001 - 1,500,000 | 7% |
| 1,500,001 - ከ2,000,000 በታች | 9% |

**ማስታወሻ፡** ይህ አሰራር የሙያ አገልግሎት ለሚሰጡ ሰዎች የሚከተሉትን ጨምሮ ለሂሳብ አያያዝ ሞያ፣ ለአርኪቴክቶች፣ ለአማካሪዎች፣ ለግንባታ ስራ ተቋራጮች፣ ለመሃንዲሶች፣ ለፋይናንስ፣ ለኢኮኖሚ እና ኢንቨስትመንት ባለሙያዎች፣ ለጤና ባለሙያዎች፤ ለህግ ባለሙያዎች ፤ ለተጨማሪ እሴት ታክስ ለተመዘገቡ ታክስ ከፋዮች እና በተጣራ ታክስ የሚከፈልበት ገቢ ላይ ግብር ለመክፈል የመረጡ የደረጃ "ለ" ግብር ከፋዮችን **አይመለከትም።**

## በጥሬ ገንዘብ ግብይት ላይ የተጣለ ገደብ (አንቀጽ 81)

ማንኛውም ግብር ከፋይ ወደ ባንክ ሂሳብ ገቢ በሚደረግ ቼክ፤ ወደ ባንክ ሂሳብ ገቢ በሚደረግ የባንክ ድራፍት፤ ከባንክ ሂሳብ ወደ ባንክ ሂሳብ ገንዘብ በማስተላለፍ ወይም በኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ ፈቃድ በተሰጣቸው የክፍያ መፈፀሚያ መንገዶች ካልሆነ በስተቀር ከዚህ በታች ለተዘረዘሩት ግብይቶች

በአንድ ቀን ውስጥ ከአንድ ሰው ጋር በተደረገ ጠቅላላ ግብይት፤ ወይም

ከአንድ ግብይት ጋር በተያያዘ የሚፈፀም ክፍያ፤ ወይም

ከአንድ ሰው ጋር ከተፈፀመ አንድ ግብይት ወይም ተግባር ጋር የተያያዘ ክፍያ ከብር 50,000 (ሀምሳ ሺ ብር) በላይ የሆነ ጥሬ ገንዘብ መቀበል አይችልም::

**ማሳሰቢያ፡** በዚህ አዋጅ አንቀፅ 81 የተደነገገውን በመተላለፍ ከተፈቀደው 50,000 (ሀምሳ ሺ ብር) በላይ በጥሬ ገንዘብ ክፍያ የተቀበለ ግብር ከፋይ በትርፍ የተቀበለውን ገንዘብ አስተዳደራዊ ቅጣት ይቀጣል::

## የኃላፊነቱ የተወሰነ የሽርክና ማህበር እና የጋራ ኢንቨስትመንት ፈንድ ግብር አከፋፈል (አንቀጽ 19(3))

በማሻሻያው አዋጅ ኃላፊነቱ የተወሰነ የሽርክና ማህበር እና የጋራ በህጋዊ መንገድ የተመዘገበ የጋራ የኢንቨስትመንት ፈንድ በማናቸውም የህግ ቅርፅ ቢቋቋምም በድርጅት ደረጃ የሚያገኘው ገቢ ግብር የማይከፈልበት መሆኑን ይደነግጋል። ሆኖም ኃላፊነቱ የተወሰነ የሽርክና ማህበር አባላት በሚከፋፈለው ገቢያቸው ላይ እንዲሁም የጋራ ኢንቨስትመንት ፈንድ በተመለከተ ባለአክሲዮኖቻቸው ከሚከፋፈሉት ትርፍ ላይ ግብር የሚከፍሉ መሆኑን ያመላክታል::

## ግብር ቀንሶ ስለማስቀረት(አንቀጽ 97 (1))

ከጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች፣ ህጋዊ ሰውነት ያላቸው አካላት፣ የመንግስት መስሪያ ቤቶች፣ ለትርፍ ያልተቋቋሙ ወይም መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና በባለስልጣኑ በሚሰጠው መመሪያ መሰረት ግብር ቀንሰው እንዲያስቀሩ ከተሰየሙት ግብር ከፋዮች በስተቀር ማንኛውም ግብር ከፋይ ለሚከተሉት ግብይቶች

- **በኢትዮጵያ ውስጥ ለሚቀርቡ ዕቃዎች፡** በአንድ የግዢ ወይም የአቅርቦት ውል ከብር 20,000 (ሃያ ሺህ ብር) በላይ ለሆኑ የዕቃ አቅርቦት የሚፈፀም ክፍያ፤
- **በኢትዮጵያ ውስጥ ለሚሰጡ አገልግሎቶች፡** በአንድ የአገልግሎት አቅርቦት ውል ከብር 10,000 (አስር ሺህ ብር) በላይ የሚፈፀም ክፍያ ከሚፈጽመው ጠቅላላ ክፍያ ላይ **3%** (ሶስት በመቶ) ግብር ቀንሶ የማስቀረት ግዴታ አለበት::

## በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ሰው ግብር የሚከፍልበት ምጣኔ ((አንቀጽ 52 (2))

በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ሰው ግብር የሚከፍልበት ምጣኔ እንደሚከተለው ተወስኗል፡-

- ጠቅላላ ክፍያ ላይ ለመድን በሚከፈል አረቦን 15% እና የሮያሊቲ 10%
- በትርፍ ድርሻ በጠቅላላ ገቢ ላይ 15%
- በወለድ ጠቅላላ ገቢ ላይ 10%
- ከሥራ አመራር ክፍያ ወይም ከቴክኒክ አገልግሎት ክፍያ ላይ ከጠቅላላ ገቢው 15%

## በትርፍ ድርሻ ላይ የሚከፈል ግብር ( አንቀጽ 57)

በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ሰው ወይም በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ሰው ሆኖ ኢትዮጵያ ውስጥ ባለው በቋሚነት በሚሰራ ድርጅት አማካይነት በኢትዮጵያ ውስጥ የትርፍ ድርሻ ገቢ ሲያገኝ በጠቅላላ የትርፍ ገቢው ላይ 15% የገቢ ግብር ይከፍላል።

## ባልተከፋፈለ ትርፍ ላይ የሚጣል ግብር ( አንቀጽ 64)

የኩባንያው የሂሳብ አመት ካለቀ በኋላ ባሉት 12 ወራት ውስጥ ለባለአክሲዮኖች ያልተከፋፈለ ወይም የኩባንያውን ካፒታል ለመጨመር ያልዋለ የተጣራ የድርጅቱ ትርፍ 15% ግብር ይከፈልበታል።

## የቅድመ ግብር ክፍያ በተመለከተ (አንቀጽ 89)

በተሻሻለው አዋጅ መሰረት፣ ደረጃ "ሀ" እና ደረጃ "ለ" ግብር ከፋዮች ባለፈው ዓመት ከከፈሉት ግብር ላይ ተመስርተው የቅድሚያ ግብር እንዲከፍሉ ይጠበቅባቸዋል።

**አሰራሩ፡-** ባለፈው ዓመት የተከፈለውን ጠቅላላ ግብር 25% በየሩብ ዓመቱ (በየሶስት ወሩ) አስቀድሞ መክፈልን ያካትታል።

**ዓላማው፡-** ለመንግስት የተረጋጋ የገንዘብ ፍሰት እንዲኖር እና በግብር ከፋዮች ላይ በዓመቱ መጨረሻ የሚፈጠርን ከፍተኛ የክፍያ ጫና ለመቀነስ ነው።

## የተወሰኑ ገቢዎች ከግብር ነፃ መሆን (አንቀጽ 68)

አዲሱ አዋጅ ከዚህ ቀደም ያልነበሩ የተወሰኑ ገቢዎችን ከገቢ ግብር ነፃ አድርጓል። ከእነዚህም መካከል፡-

- በኢትዮጵያ የተቀማጭ ገንዘብ መድን ፈንድ የሚሰበሰበው አረቦን (Premium)፣
- በስራ ላይ ያሉ ኩባንያዎች አዲስ አክሲዮን በማውጣት የሚያገኙት የካፒታል ዋጋ እድገት ጥቅም (ፕሪሚየም)፣
- ማናቸውም ኩባንያ በኩባንያው ውስጥ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ከ12.5% ያላነሰ ድምፅ የመስጠት መብት እና ኩባንያውን ውሳኔዎች የመቆጣጠር መብት ላለው በኢትዮጵያ ነዋሪ ለሆነ ኩባንያ የሚፈፅመው የአክሲዮን ትርፍ ድርሻ ክፍያ፤

## የቋሚ የሥራ ቦታ ትርጉም ማሻሻያ (አንቀጽ 4)

አንድ የውጭ ኩባንያ አገልግሎት ለመስጠት በኢትዮጵያ ውስጥ የሚቆይበት ጊዜ ከ183 ቀናት (6 ወራት) በማሻሻያው አዋጅ ወደ 91 ቀናት (3 ወራት) ዝቅ አድርጎታል። ይህ ማለት የውጭ ኩባንያዎች በኢትዮጵያ ውስጥ የሚያከናውኑት የአገልግሎት ወይም የፕሮጀክት ስራ ከ91 ቀናት በላይ ከቆየ፣ በኢትዮጵያ "ቋሚ የሥራ ቦታ" እንዳለው ተቆጥሮ በኢትዮጵያ ውስጥ በሚያገኘው ገቢ ላይ ግብር የመክፈል ግዴታ ይኖርበታል። ይህ ለውጥ በተለይ ከአማካሪ ድርጅቶች፣ ከኮንስትራክሽን እና ከሌሎች የአገልግሎት ሰጪ የውጭ ኩባንያዎች ጋር ለሚሰሩ የሀገር ውስጥ ንግዶች ጠቃሚ መረጃ ነው።

## የግብር ማበረታቻዎች በአንድ ህግ ስር መሆን (አንቀጽ 105)

በማሻሻያው አዋጅ፣ ማንኛውም የገቢ ግብር ማበረታቻ (ለምሳሌ፣ የግብር በዓል) ሊሰጥ የሚችለው በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣው የኢንቨስትመንት ማበረታቻ ደንብ መሰረት ብቻ እንደሆነ ይደነግጋል። በሌሎች ልዩ አዋጆች ወይም ደንቦች የተሰጡ የገቢ ግብር ነፃ መብቶችን ሽሯል። ይህ የግብር ማበረታቻ አሰጣጥን ወጥ እና ማዕከላዊ ያደርገዋል። ባለሀብቶች የማበረታቻ መብቶቻቸውን ለማወቅ ወደ ተለያዩ ህጎች መመልከት ሳያስፈልጋቸው በአንድ ዋና ደንብ ስር እንዲጠቃለል ያደርጋል።